transform nutrition

research brief

ISSUE 05 | MARCH 2015

# የሥርዓት-ምግብን ችግር ለመቀነስ አስተዋፅኦ ያደረጉ ወሳኝ ሁነቶችና በድህረ የምዕተ-ዓመቱ ግብ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት

የምዕተ-ዓመቱ ግብ ዘመን እየተገባደደ፤ የፈረንጆቹ 2016 - ድህረ የምዕተ-ዓመቱ ግብ እየተቃረበ ባለበት ጊዜ የህፃናትን የሥርዓት-ምግብ ችግር የመቅረፍ ጉዳይ በዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳዎች ትልቅ ትኩረት እየተሰጠው ይገኛል። ይህንን ችግር መቀነስ እንደ አንድ ዋነኛ የልማት አመላካች ብቻ ሳይሆን እንደ ልማት አምጭም ተደርጎ እየተወሰደ ነው። ይህ አጭር ፁሑፍ ከ1970-2012 እኤአ በ116 አገሮች የህፃናትን የሥርዓት-ምግብ ችግር ለማሻሻል አስተዎፅኦ ያደረጉ ጉዳዬችንና ለወደፊቱ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራትን ለይቶና አጥንቶ በ2015 ‘ወርልድ ዲቨሎፕመንት` ያሳተመውን ፁሑፍ በአጭሩ ያቀርባል።

ጥናቱ እንደሚያሳየው ባለፉት ጊዜያት ለመቀንጨር (stunting) መቀነስ በዋናነት አስተዋፅኦ ያደረጉት የንፁህ ውሃ አቅርቦትና የንፅህና አጠባበቅ፤ የሴቶች ትምህርት፤ የፆታ እኩልነትና በየአገሮቹ ምግብ በጥራትና በብዛት መገኘት ናቸው። የገቢ በየዕለቱ ማደግ እና የአስተዳደር ሁኔታዎች መሻሻል ይህንን በማቀላጠፍ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ለወደፊቱም ቀጥተኛ ከሆኑ የሥርዓት-ምግብ (nutrition specific) ፕሮግራሞችና ከሥርዓት-ምግብ ጋር ተጓዳኝ የሆኑ (nutrition sensitive) ፕሮግራሞች እና ፖሊሲዎች ጎን ለጎን የሥርዓት-ምግብ ችግር ቅነሳን ለማሳለጥ በቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ በእነዚህ ተግባራት ላይ የበለጠ መስራትን ይጠይቃል።

የህፃናትን ሥርዓት-ምግብ ችግር በመቀነስ በታዳጊ አግሮችም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ እስካሁን የታየው ተነሳሽነት ትልቅ የሚባል ደረጃ ደርሶ አያውቅም። በዚህ ምክንያት እንዴት የሥርዓት-ምግብ ችግርን መቀነስ እንችላለን ለሚለው ጥያቄ መልስ በሰፊው ይፈለግ ነበር። ላለፉት አሥርት ዓመታት ተገቢነት ያላቸው ቀጥተኛ የሆኑ የሥርዓት-ምግብ ፕሮግራሞችን መለየት ለምሣሌ ጥቃቅን ንጥረ ምግቦችን በተጨማሪ ማደል፤ የእናት ጡት ወተት ማጥባትን ማበረታታትን እና የልማት ፕሮግራሞች የበለጠ ሥርዓት-ምግብን አካታች እንዲሆኑ ማድረግ ትኩረት የተሰጣቸው አብይ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ዋና አላማው ለህፃናት መቀንጨር መንስኤ የሆኑትን በማጥናት እያደገ ለመጣው መረጃን መሰረት ያደረገ ትግበራ አስተዋፅኦ ማበርከት ሲሆን ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ስራዎችን በመለየት ለድህረ የምዕተ-ዓመቱ ግብ አጀንዳ ቀረፃና ትግበራ መረጃ ማቅረብ ነው።

በእነዚህ መንስኤዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ፕሮግራሞች የግድ ሥርዓት-ምግብ ተኮር ላይሆኑ ይችላሉ ነገር ግን ደግሞ መቀንጨርን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና ሊኖ ራቸው ይችላል፤ ምክንያቱም ለስርዓት-ምግብ ችግር መሰረታዊ መንስኤዎች ናቸው ተብለው በተለዩ ጉዳዩች ላይ ጭምር ስለሚሰሩ፡፡

## የጥናቱ ግኝቶች

ጥናቱ በህፃናት ሥርዓት-ምግብ ችግር በመጪዎቹ 10 ዓመታት የህፃናትን መቀንጨር መጠን በፍጥነት



AMERTI LEMMA/SAVE THE CHILDREN

የ20 ዓመቷ ወጣት ፋጡማ ከ7 ወር ልጇ ከመሀመድ ጋር በቤተሰቦቿ ቤት

ለመቀነስ በፖሊሲ ስትራቴጂዎች ሊታሰቡ የሚገባቸውን ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት ለመንግስታት እና ለዓለም አቀፍ የልማት ድረጅቶች ግልፅ የሆነ አቅጣጫ ያሳያል። የፖሊሲ ስትራቴጂዎችም በሚከተሉት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ይመክራል፡፡

- በብሔራዊ ደረጃ በቂ ምግብ እንዲኖር በማድረግና ምግቦችን በቂ በሆነና ጥራት ባለው መልኩ የተሟላ የስርዓት-ምግብ ይዞታ እንዲኖራቸው በማድረግ የምግብ ዋስትናን ማሳደግ፤
- የንፁህ ውሃ አቅርቦትን፣ የግል እና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን በማሳደግ የጤና ከባቢያዊ ሁኔታን ማሻሻል፤

- የሴቶችን ትምህርትና የፆታ እኩልነት በማሳደግ ለህፃናት የሚደረጉ እንክብካቤዎችን ማሻሻል፤

እነዚህን ስድስት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች ለወደፊቱ የመቀንጨር ስፋትን ለመቀነስ የሚኖራቸውን አቅም ከግምት ውስጥ አስገብተን በደረጃ ስናስቀምጣቸው ፡-

- የንፅህና አጠባበቅ ተደራሽነት እና የሴቶች ትምህርት ሁኔታ የቀዳሚነት ደረጃውን ሲይዝ፤
- የንፁህ ውሃ ተደራሽነት፣ የፆታ እኩልነት፣ በብሔራዊ ደረጃ የምግብ አቅርቦት ዝቅተኛውን ደረጃ ይዘዋል፡፡እነዚህ በዝቅተኛ ደረጃ የተቀመጡት ግን ከሴቶች የትምህርት ሁኔታ ጋር ተያያዥነታቸው ጎላ  ያለ ነው፡፡

ጥናቱ የኢኮኖሚ እድገትና ምቹ አስተዳደር እነዚህን ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ተግባራትን ለማስፋት ሊደግፉ የሚችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በኩል ያላቸውን ጠቀሜታ አጉልቶ ያሳያል፡፡

የገቢ ማደግ፣ የንፅህና አጠባበቅ ተደራሽነት፣ የሴቶችን ትምህርትና በየሀገራቱ ያለን የምግብ አቅርቦትን በመደገፍ የህፃናትን መቀንጨር እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

ምቹ አስተዳደር የንፁህ ውሃ አቅርቦትን በማሳደግ ረገድ ውጤቱ ከፍተኛ ነው፡፡

የቀነጨሩ ህፃናት በብዛት ባሉባቸው በደቡብ ኢስያ አገራት እና በሰብ-ሰሃራን አፍሪካ አካባቢዎች ላይ የተሰራው ይህ ጥናት የሚከተሉትን ውጤቶች ይዞ ወጥቷል፡፡

- በደቡብ ኢስያ አገራት የሴቶች ትምህርትና የምግብ አቅርቦት ተከታታይ በሆነ መልኩ መሻሻል እንዳለበት ሆኖ  ቀሪዎቹ ሶስቱ ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ግን የተለየ ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡ እነሱም የንፅህና አጠባበቅ ተደራሽነት፤ በስርዓተ-ምግብ የበለፀጉ ምግቦች በየሀገራቱ የመገኘት ሁኔታና የፆታ እኩልነት ናቸው፡፡



KARIN BEATE NOSTERUD/SAVE THE CHILDREN

በሶማሌ ክልል የሊበን ወረዳ ነዋሪዋ እናት ከቤቷ በር ላይ ተቀምጣ እህል ከግርዱ እየለየች

- በሰብ-ሰሃራን አፍሪካ ሀገራት ጥናቱ የንፅህና አጠባበቅ፣ የሴቶች ትምህርትና የፆታ እኩልነት ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ተግባራት እንደሆኑ አመላክቷል፡፡

እነዚህ ሁለቱ የዓለማችን አካባቢዎች ከሌሎች ታዳጊ አገሮች ጋር ሲነፃፀሩ ብሔራዊ ገቢያቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለዚህም ተከታታይነት ያለው የገቢ ማሳደግ ሥራ የህፃናትን መቀንጨር ለመቀነስ ሚናው የጎላ ነው፡፡

የአስተዳደርን ጥራት ማሻሻል ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም በደቡብ ኢስያ አገራት የፖለቲካዊ መረጋጋትን ትኩረት በሰጠ መልኩ፤ በሰብ-ሰሃራን አፍሪካ ሀገራት ደግሞ የአስተዳደር ውጤታማነትንና ከሙስና የፀዳ አሰራር መከተልን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

## ማጠቃለያ

ከላይ የቀረቡት ስድስቱ የህፃናትን መቀንጨር ለመቀነስ ወሳኝ የሆኑ ሁኔታዎች ከቀጥተኛ ስርዓተ-ምግብ ፕሮግራሞች ጎን ለጎን በፍጥነት መተግበር ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተከታታይነት ያለው የገቢ ማደግና መልካም አስተዳደር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ የስርዓተ-ምግብና ሰፊው የልማት ማህበረሰብ እነዚህን ወሳኝ ጉዳዮች በፍፁም ችላ ሊላቸው አይገባም፡፡ ምክኒያቱም የህፃናት ሞት እንዳይከሰት ለመከላከል፣ የሰብዓዊ አቅምና ግብዓት በከንቱ እንዳይባክን ለመከላከልና በስርዓተ-ምግብ ችግር ምክኒያት ከሚመጣ የልማት መደናቀፍ ለማምለጥ ቁልፍ መሳሪያዎች ስለሆኑ፡፡

## ለተጨማሪ ንባብ


L Smith, L Haddad Reducing Child Undernutrition: Past Drivers and Priorities for the Post-MDG Era. World Development, Volume 68, April 2015, Pages 180–204 http://www.sciencedirect.com/science/article/pii/S0305750X14003726.

Haddad, L. 2013b. How should nutrition be positioned in the post-2015 agenda? *Food Policy*, 43, 341-352.

Lancet. 2013. Executive summary of the Lancet Maternal and Child Nutrition Series. *The Lancet*, June 6, 2013.

UNICEF. 2013. Improving child nutrition: The achievable imperative for global progress. New York: United Nations Children's Fund.


## እውቅና


This research brief is based on a paper funded by Transform Nutrition and published in World Development *Reducing Child Undernutrition: Past Drivers and Priorities for the Post-MDG Era* by Lisa Smith from TANGO International and Lawrence Haddad from IFPRI, April 2015.



በኢትዮጵያ ትራንስፎር ኒውትሪሽንን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የፕሮግራሙ ተጠሪዎችን ያግኙ፡-

ቀናው ገብረስላሴ፣ ኮሚኒኬሽንና ሪሰርች አፕቴክ ማናጀር፣ ትራንስፎር ኒውትሪሽን፣
ሴብ ዘ ችልድረን - ኢትዮጵያ ኢሜል፡- Kenaw.gebreselassie@savethechildren.org
ስልክ፡-+251-113-720030/+251-910-808737

ጆን ሆዲኖት፣ በኢትዮጵያ የትራንስፎር ኒውትሪሽን ጥናትና ምርምር መሪ
ኢሜል፡- jfh246@cornell.edu



ትራንስፎር ኒውትሪሽን በእንግሊዝ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰራ የጥናት ፕሮግራም ሲሆን የአምስት ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር እና የልማት አጋር ድርጅቶች ጥምረት ነው። እነሱም:- ኢንተርናሽናል ፉድ ፖሊሲ ሪሰርች ኢንስቲቱት፣ ኢንስቲቱት ኦፍ ዴቨሎፕመንት ስተዲስ፣ ኢንተርናሽናል ሴንተር ፎር ዲያሪያል ዲዚዝ ሪሰርች ባንግላዲሽ፣ ፐብሊክ ሄልዝ ፋውንዴሽን ኦፍ ኢንዲያ እና ሴቭ ዘችልድረን ናቸው፡፡


**ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረገ መረጃ በመጠቀም የሥርዓተ-ምግብ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ሥራዎች እንዲሰሩ እናበረታታለን፡፡**


እዚህ የተገለፁት ሐሳቦች የእንግሊዝ መንግሰትን ኦፊሴላዊ ፖሊሲዎችን አያንፀባርቁም፡፡



ድረ-ገፃችንን ይጎብኙ፡- www.transformnutrition.org ኢሜል፡ transform@ids.ac.uk ቲዩተር፡- @TN_NutritionRPC